

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።
አንድነቱን ሶስትነቱ ሳይከፋፍለው ሶስትነቱን በአንድነቱ ሳይጠቃለል በአንድነቱና በሶስትነቱ ፀንቶ የሚኖር በባህሪው የማይመረመር ሲሆን በፍጥረቱ የሚታወቅ መባርቅትን በነፀብራቅ ብልጭልጭታ የሚበትን ውሆችን በረቂቅ ደመና አካል የሚቋጥር ሊወድቁ የሚፍገመገሙትን የሚደግፍ ሀሰተኞችን ወደ እውነት የሚመራ እሩህሩህ አምላካችን እግዚአብሔር ስሙ ለዘላለም ይባረክ
የእናታችን የእመቤታችን የድንግል ማርያም ስም በትውልዱ ሁሉ አንደበት የተመሰገነ ይሁን ። አሜን
(Dawit demessie)
" የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና በሥጋ ምኞትም በስካርም በዘፈንም ያለ ልክም በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃል።" (1ጴጥ4:3)
"በክርስቶስ ላላችሁ ለሁላችሁ ሰላም ይሁን"።

☞†† ትምህርተ ንስሐ ††☜

ስለ ንስሐ ከመነጋገራችን በፊት የንስሐ አባት መያዝ ለምን ያስፈልጋል???
ጌታችን " በወንጌል በቀን የሚሄድ ሰው አይሰናከልም የዚህን አለም ብርሃን ያያልና በጨለማ የሚሄድ ግን ይሰናከላል!!" ብሎ ተናግሯል:: የዚህ ቃል ትርጉም አንድም በምክረ ካህን በ ፈቃደ ካህን የሚኖር ሰው ነፍሱ ከሃጢአት እንደምትጠበቅ ያስረዳል። የዚህ አለም ብርሃን የተባሉት ጌታችን “እናንተ የአለም ብርሃን ናችሁ” ያላቸው ካህናት ሲሆኑ "በቀን የሚሄድ" የተባለው ደግሞ በምክረ ካህን የሚኖር ሰው ነው። ስለንስሀ አባት ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ
"የንስሀ አባት ማለት እርሱን ስትመለከት እግዚአብሔርን እና ትዕዛዛቱን የምታስታውስበት ሰው ማለት ነው።" ብለዋል

• በወንጌል “ ለወይን ስፍራዉ ሰራተኞችን ይቀጥር ዘንድ በማለዳ ወጣ በአስራ አንድ ሰአትም ቀጠረ” የሚለዉ ምሳሌ፡ ማለዳ በተባለ የልጅነት እድሜ ላይ የሚጠብቅ የሚኮተኩት መምህረ ንስሃ መያዝ እንደሚያስፈልግ ያሳያል። ዕድሜያችን ለሀጢአት በደረሰችበት ቅፅበት ለንስሃም(ለ ኑዛዜም) ትደርሳለችና።

• በሲራክ 6÷6 ላይ “ብዙ ሰዎች ወዳጆች ይሁኑህ ከብዙዎች አንዱ ምክርህን የምትነግረው ከልቡናህ ጋር አንድ ይሁን።” የሚለው ቃል ምእምናን ስለ ሐይማኖትና ምግባር የሚያስተምሯቸው ብዙ ካህናት ሊኖሩዋቸው ቢችሉም ከብዙዎች አንዱ ግን ንስሃቸውን የሚናዘዙለት መምህረ ንስሃ ሊሆናቸው እንደሚገባ ያጠይቃል።

• አዳም በገነት ለሰባት አመታት ከቆየ በሁዋላ በዲያቢሎስ ተፈትኖ እንደወደቀ፡ በሃጢያት መፈተንና መዉደቅ ለሰው የሚፀናበት ዕድሜ ከሰባት አመት ጀምሮ ስለሆነ ወደ ንስሃ አባት መቅረብ ይኖርበታል።

• በምክረ ካህን መኖር ራሱ ትልቅ መንፈሳዊ ማእረግ ነው የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ከብሉይ ኪዳን ሰዎች የሚከብሩትን ያህል በምክረ ካህን የሚኖሩ ምእምናን ከአማኒያን በላይ የከበሩ ናቸዉ።

• ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ 12 አመቱ ከመምህራን ጋር መገናኘቱ እኛም ከልጅነታችን ጀምሮ ከ መምህራን አባቶች ጋር እነድንገናኝ አብነት ይሆን ዘንድ ነዉ ማቴ20-2

✡ ✡☞"ሀጢያትን መናዘዝ ለምን አስፈለገ " ???☜✡✡

ሀጢያትን ለእግዚአብሄር በካህን በኩል መናዘዝ መፅሃፍ ቅዱሳዊ መሰረት ያለዉ ጠቃሚ ጉዳይ ነዉ። እግዚአብሄር አዳም በበደለ ጊዜ “አዳም ሆይ ወዴት ነህ?” ብሎ የጠየቀዉ አዳም እንዲናዘዝ ስለፈለገ እንጂ አዳም ያደረገዉን ሳያዉቅ ቀርቶ አልነበረም:: “እምቅድመ ይፍጥሮ ለአዳም የአምር ግብሮ” ”አዳምን ከመፍጠሩ በፊት ስራዉን ያዉቃል” እንዲል። አዳምም እግዚአብሄር በጠየቀዉ ጊዜ ”ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ” በማለት ተናዝዋል። ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ቦታዎች ሰዎች ሀጢያታቸዉን ይናዘዙ እንደነበር በመፅሀፍ ቅዱስ ተገል ል። ሐዋ 19-18 ፡ማቴ3 5-6 ፡ዘሌ 5-16፡ ኢያ 2- 19። ይሁን እንጂ “ሀጢያቴን ለመተዉ ከፈቀድኩ አይበቃም ወይ? መናዘዙ ለምን አስፈለገ?” የሚሉ ሰዎች አሉ ሀጢያትን በካህን ፊት መናዘዝ ግን የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡-

❖ ሀጢያትን በዝርዝር በካህን ፊት መናዘዝ ዳግመኛ በዚያ ሀጢያት ላለመያዝ ሀይልን ይሰጣል። ቅዱስ ዮሃንስ አፈወርቅ “በበደሉ ላይ ድፍረትና ሽንገላን

የሚጨምር (ሀጢያት ሰርቶ እንዳልሰራ ዝም የሚል) ከዚያች ሀጢያት መጠበቅ አይችልም። እርስዋን በምትመስል ሀጢያት ከመዉደቅም አይድንም" እንዳለ።

❖ ንጉስ የሚሸረዉና የሚሾመዉን ግራና ቀኝ አቁሞ የሚሸረዉን ወቅሶ የሚሾመዉን አሞግሶ እንደሚያከብር ያለፈ ሀጢያታችንን በካህኑ ፊት ስንዘረዝርም ያለፈዉን ሀጢያታችንን ሸረን በሚመጣዉም ህይወት ያንን ሀጢያት ላለመድገም እየወሰንን ነው።

❖ ኑዛዜ ያሳቅቃል። መሳቀቁ ደግሞ ለሰራነዉ ሀጢያት ዋጋ ነዉ። በፍርድ ቀን ጌታ በሰማይ መላእክት ፊት ሀጢያታችንን ገልጦ ከሚያሰቅቀን ይልቅ እኛዉ እራሳችን እዚሁ እንደኛዉ ደካማ ሰዉ በሆነው በካህኑ ፊት በመናዘዝ ለሰራነው እጅግ ግዙፍ ሃጢያት የምንቀበለው ኢምንት ቅጣት ነው።

❖ በሽታውን የደበቀ መድሃኒት የለውም እንደሚባለው የነፍሱን ደዌ ሀጢያቱን የሚደብቅም እንዲሁ መፍትሄ አያገኝም። የካህኑን ፀሎትና ምክርም ያጣል። "ሀጢያቱን የሚደብቅ /የሚሰውር አይለማም፡ የሚናዘዛትና የሚተዋት ግን ምህረትን ያገኛል" እንደተባለ ።ምሳ8-13
ሀጢያታችንን ለምን በቀጥታ ለእግዚአብሄር ብቻ አንናዘዝም??

❖ ሀጢያትን ለካህን መናዘዝ ለእግዚአብሄር አለመናዘዝ አይደለም። ሀጢያትን ለካህን መንገር ለእግዚአብሄር መናዘዝና ክብር መስጠት ነው። እያሱ እንዳለ "ልጄ ሆይ ለአምላክ ክብርን ስጥ፡ ለእርሱም ተናዘዝ፡ ያደረግከውንም ንገረኝ አትሸሸገኝ" ኢያሱ 7-19። ኢያሱ "ክብርን ስጥ" ያለው ለእግዚአብሄር: "ተናገር" ያለው ግን ለራሱ መሆኑ ሀጢያትን ለካህን መናዘዝ ለእግዚአብሄር ክብር መስጠት እንደሆነ ያሳየናል። አበዉ ካህናትም ኑዛዜን ከተቀበሉ በኋላ "እግዚአብሔር ይፍታህ" እንጂ "ፈትቼሃለሁ " አይሉም። ይህም ምንም በነሱ ፊት ብንናገርም ሰሚዉም ሆነ በእነርሱ እጅ ስርየት የሚሰጠዉ እርሱ ባለቤቱ ስለሆነ ነው። "ሁለት ወይም ሶስት በሚሆኑበት በዚያ በመካከላችሁ እገኛለሁ" ብሎ ቃል የገባ አምላክ በእናዛዚው ካህንና በተናዛዚው ምእምን መካከል ሆኖ ይሰማል፡ ስርየትንም ይሰጣል።

❖ ሰው ሲታመም ሀኪም ቤት ሄዶ በሀኪሙ ፊት "ቆረጠኝ ወጋኝ. . . " እያለ ህመሙን እንደሚያብራራው ሁሉ፡ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያሉት ካህናትም የነፍስ ሀኪሞች ናቸውና እያንዳንዱን የነፍስ በሽታ (ሀጢያት) በዝርዝር በእነርሱ ፊት ልንናዘዝ ይገባል። በሀኪሙ ፊት ምንናዘዘው የእግዚአብሔርን ፈዋሽነት ክደን እንዳልሆነው ሁሉ በካህናት ፊት የምንናዘዘውም የእግዚአብሔርን ሰሚነት ክደን አይደለም።

❖. ለምን በቀጥታ ለእግዚአብሔር አልናዘዝም ማለት በራሱ ትዕቢት ነው። ንስሃ የሚገባ ሰው ሊል የሚገባው "ከበደሌ ብዛት የተነሳ ቀና ብዬ የሰማይን ርዝመት አይ ዘንድ እንኩዋ አገባቤ አይደለም" ነው(ፀሎተ ምናሴ)።

❖• በወንጌል እግዚአብሔር "እርስ በርሳችሁ ሀጢያታችሁን ተናዝዙ" ያለው የሰው ልጅ ከፈጣሪ ይልቅ ሰውን ስለሚፈራና ስለሚያፍር በሃጢያቱ እንዲሳቀቅ ስለፈለገ ነው። እግዚአብሔር ያየኛል ይሰማኛል ሳይል የሰራውን ሀጢያት እንዴት እግዚአብሔር ያየኛል ይሰማኛል ብሎ ይናዘዛል? እነዚህ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን የሚፈሩትን መጽሐፍ እንዲህ ይላቸዋል "እስመ ዐይነ ሰብእ ያፈርሆሙ ወኢየአምሩ ከመ አይነ እግዚአብሔር ያበርህ እምእዕላፍ ፀሀይ" "የሰው ዐይን ያስፈራቸዋል: የእግዚአብሔር አይን ግን ከብዙ አእላፍ ፀሀያት ይልቅ እንደሚያበራ አያውቁም!!!"

★★★ "ንስሐ ማለት ምን ማለት ነው?"★★★

ንስሐ ማለት አንድ ሰው በሠራው ጥፋት፣ ባደረገው ስህተት፣ በፈጸመው ኃጢአት ማዘኑና መቆርቆሩ፣ መፀፀቱ፣ ዳግመኛም ያንን የመሰለ ኃጢአት ላለማድረግ የሚወስነው ውሳኔ ነው። በአጭሩ ንስሐ ማለት ትርጉሙ ይህ ሲሆን ፤ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ደግሞ
መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስገነዝበን ቀጥሎ የተጠቀሱትን ፍችዎች ያጠቃለለ ሆኖ እናገኘዋለን።
↪ ንስሐ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው። 《ሚልኪያስ 3፡7》

↪ ንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ነው። 《2 ቆሮንቶስ 6፡19》

↪ ንስሐ ከኃጢአት እንቅልፍ መንቃት ነው። 《ሮሜ 13፡11》

↪ ንስሐ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት መመለስ ነው። 《ኤፌሶን 5፡14》

↪ ንስሐ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ እግዚአብሔርን የሚያስወድድ ከንጹህ ልብ የሚመነጭ ጸጋ ነው። 《ሕዝቅኤል 36፡25-27》

➲ ንስሐ ከኃጢአትና ከዲያቢሎስ ባርነት ነጻ መውጣት ነው። ﴿ዮሐንስ 8፥34-36﴾

➲ ንስሐ ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ስለ ቅድስና ብሎ ኃጢአትን መተው ነው። ﴿ምሳሌ 28÷13﴾

➲ ንስሐ ኃጢአትን ከተዉ በኋላ በፍጹም መልሶ አለመስራት ነው።

➲ ንስሐ ስለ አለፈው ስህተት አብዝቶ ማልቀስ፤ ያለፈውን የኃጢአት ኑሮ ማውገዝና መኮነን ነው። ﴿ኢዩኤል 2፡12﴾

➲ ንስሐ ፍጹም የሆነ የሕይወት ለውጥ እንጂ ጊዜያዊ ስሜት አይደለም፤ ﴿ሮሜ 12፡2﴾

➲ ንስሐ ኃጢአትን ሲሠሩ ከመኖር ይልቅ ከእግዚአብሔር ጋር መኖርን መሻት ነው። ﴿መዝ 73፡28﴾

➲ ንስሐ የአዕምሮ መታደስ ነው። ﴿ሮሜ 12፡2﴾

➲ ንስሐ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ የሚያስችል ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር የሚያስገባ ቁልፍ ነው። ﴿ማቴ 25÷1-13﴾

➲ ንስሐ በቀራንዮ መስቀል ላይ እኛን ለማዳንና ከኃጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት የፈሰሰልንን የክርስቶስን ደም እንድናስብ የሚያደርግ መንፈሳዊ ሃብት ነው።

➲ ንስሐ ከኃጢአት የሚያነጻ ሱራፌል ከመንበረ ሥላሴ የወሰዱት የእሳት ፍም ነው። ﴿ኢሳ 6፡4﴾

➲ ንስሐ ከሚመጣው የመጨረሻ መከራና ሃዘን መዳኛ ወይም ማምለጫ መንገድ ነው። ﴿ዮናስ 3፡10﴾

➲ ንስሐ እግዚአብሔር የሰውን ኃጢአት ይቅር የሚልበትና ከኃጢአት ውጤት የሚያድንበት መሳርያ ነው።

➲ ንስሐ ከሰዎች ጋር ለመታረቅ የተዘረጋ የእግዚአብሔር እጅ ነው። ﴿መዝሙር 50/51﴾

➲ ንስሐ እግዚአብሔር ወደ ሰው የሚጣራውን ጥሪ ሰምቶ ወደ እርሱ መመለስ ነው። ﴿ዮሐንስ 7፡51﴾። ﴿ኤፈሶን 4፡30﴾

➲ ንስሐ ስለ አለፈው ኃጢአት በተሰበረ ልብ መፀፀት ነው። ﴿መዝ 50/51÷17﴾

➲ ንስሐ ሰዎች ስለ ኃጢአታቸው ተፀፅተው ከእግዚአብሔር ጋር እንዳይታረቁ በብርቱ በሚጥረው ሰይጣን ላይ ድልን የሚያስገኝ ነው። ﴿መዝ 123/124÷6-7﴾:: እናም ንስሀ ሀጥኡን ፃድቅ ዘማዊውን ድንግል፣ቀማኛውን መፅዋች የሚያደርግ ደግኛ ስርአት ነው። በመሆኑም ስለንስሀ በስፋት ና በጥልቀት ማወቅ ለሁላችንም የሚያሻ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም በዘመኑ ያለነው ክርስቲያኖች ግን በዚህ መንፈሳዊ ጉዞ ውስጥ እንብዛም ነን ስለንስሀ እናውቃለን እንጂ ንስሐ አንገባም ለዚህም ይመስለኛል ከብዙ የክርስቲያኖች ህይወት የጎላ መንፈሳዊ ለውጥን ማየት አዳጋች የሆነው ።ሀጢአት የሌለበት ማንም የለም 1ዮሀ 1፥8 ነገር ግን አንድ ጥያቄ አለ እርሱም "ልትድን ትወዳለህን "ዮሀ 5፥6 የሚል ከወደድክ የመዳንቀን አሁን ነው 2ቆሮ6፥2 ሰለዚህ የመዳን ፍላጎጎት ካለን በምድር ላይ ሀጢአት የማስተሰረይ ስልጣን ወደተሰጣቸው አባቶች መሄድና በደላችንን ሁሉ መናዘዝ ይገባል። ማቴ9፥6 ቁጥር ከዜሮ እንዲጀምር ንስሐም ሀጢአትን ከመተው ከመጥላት ይጀምራል እስከ ፍፁምነት እስኪደርስ ነገር ግን የንስሀ ፍፁምነት ሀጢያትን ከመጥላት የሚመጣ ነው ተነሳሂው ልቦናው ሀጢአትን ፈፅሞ መጥላት ደረጃ ላይ ሲደርስና ይህ ጥላቻው ከባህሪው ጋር ተስማምቶ የሚቆይበትን መንገድ ላለማጨናገፍ ሲችል ይህ ሰው ወደ ንፅህና ደርሷል እንላለን በዚህ የቅድስና ጉዞአችን ውስጥ ግን ዲያቢሎስ አንድም ንስሐ በገባንባቸው ሌላ ጊዜ ደግሞ ቀድሞ በማናውቃቸው ሀጢአቶች መዋጋቱን አያቆምም የቅዱስ ክርስቲያን ልዩ ነቱ ግን በወደቀበት አለመቅረቱ ነው። ፃድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ይነሳማል ምሳ24፥17 የሚለውን ቃል ያስባል ልክ እንደ ሚክያስ" ጠላቴ ሆይ፥ ብወድቅ እነሣለሁና፥ በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ። "(ት.ሚክ 7:8) ይላል። ምንም እንኳን ሀጢአት ብንሰራም ከሀጢአት በላይ መሆን እስክንችል ድረስ መናዘዝ ይገባናል።
"የምንወደው ጓደኛችን ቢሞትብን ለቀናት ሐዘን እንቀመጣለን። ብር ቢጠፋብንም እንዲሁም እንቆጫለን። ዕለት ዕለት ሐጢአት ስንሠራ ግን ጥቂትስ እንኳ አናስብም :: መቼ ይሆን የምንነቃው?
ልብስ የተሰጠን ከብርሃናዊ ልብሳችን ስለተራቆትን ነው /ዘፍ. 3፥20/። ታድያ በኃጢአታችን ምክንያት በተሰጠን ልብስ ልባችንን

ከፍ ከፍ የማናደርገው ስለምንድ ነው?
ተወዳጆች ሆይ! እስኪ ንገሩኝ ከእኛ መካከል የሚኖርበትን ቤት በቆሸሸ ቁጥር የማያጸዳው ማነው?ታድያ የእግዚአብሔር
ማደርያ የኾነው ሰውነታችንን በንስሐ መወልወያ የምናጸዳው መቼ ነው?
ልጆቼ ንስሐ ግቡ እንጂ በኃጢአታችሁ ምክንያት በፍጹም ተስፋ አንዳትቆርጡ። (ቅዱስ ዮሀንስ አፈወርቅ)
ሀጢያትን ግን በድፍረት እንዳንሰራ ማር ይስሀቅ እንዲህ ይላል "እጠገናለሁ ብሎ
መሰበር እንዳይመች ንስሃ እገባለሁ ብሎ ሀጢአት መስራት አይገባም " ስለንስሀ
ይህን ያክል ካልን የንስሀ ጥቅም ምንድነው?

❀❀❀ "የንስሀ ጥቅም " ❀❀❀

(ሀ)•የአእምሮ ነፃነት ለማግኘትና ጭንቀትን ለማስወገድ ይረዳል።

(ለ)•ንስሐችንን በምንናዘዝበት ወቅት ለሀጢአታችን ስርየት እናገኛለን።

(ሐ)•ንስሐ ስንገባ ለቅዱስ ቁርባን የተገባን እንሆናለን ከሁሉ በላይ ክርስቶስ በእኛ
ውስጥ እንዲኖር እናደርጋለን 1ቆሮ11፥28

(መ)• በንስሀ ነፍሳችንን እንመረምራለን እናነፃማለን ሰለዚህ መንፈሳዊ ህይወታችን
እናሻሽላለን።

(ሠ)•ሀጢአትህን ለመምህረ ንስሐ በተናዘዝክ ጊዜ በተናዘዝከው ሀጢአቶችላይ
ለማሸነፍ ሀይልን ታገኛለህ። ታላቁ መቃርዮስ አንድ ጊዜ ሰይጣንን አግኝቶት "በበረሀ ካሉት መነኮሳት ጋር
በምታደርገው ውጊያ ዙሪያ ስራህ እንዴት ነው?" በማለት ይጠይቀዋል። ሰይጣንም
መልሶ "በጣም መጥፎ ነው ምንም እንኳን ክፉ ሀጢአቶችን እንዲሰሩ
ባላሳስባቸውም የእኔ ጓደኛ ከሆነው ከአንዱ መነኩሴ በስተቀር ሁሉም
ያሳሰብኳቸውን ሀጢአት ለመምህረ ንስሐቸው ይነግራሉ። ይህ የእኔ ጓደኛ ነው
ያልኩት መነኩሴ ግን ሀጢአቱን አይናዝዝም" አለው ። ከዚህ በኋላ ቅዱስ
መቃርዮስ ወደዚህ መነኩሴ ሄዶ ሀጢአቱን ለመምህረ ንስሐው እንዲናዘዝ
መከረው ያ መነኩሴም በየጊዜው መናዘዝ ጀመረ። ከዚህ በኋላ ቅዱስ መቃርዮስ
ሰይጣንን አግኝቶ እንደ ቀድሞው ያለ ጥያቄ ጠየቀው ። ሰይጣንም መልሶ
"አሁንማ ስራዬ በጣም መጥፎ ሆኗል ያ ጓደኛዬ የምለው መነኩሴ እንኳን
ሀጢአቱን ለመምህረ ንስሐው በመናዘዝ ጠላቴ ሆኗል " አለው። ሰለዚህ እኛም
ልናሳፍረው ይገባል

(ረ)• በንስሀ ለችግራችን መፍትሄ እናገኛለን ሉቃ17፥11-14

(ሰ) •ሌላውና የመጨረሻው መንፈሳዊ ጥቅም የእግዚአብሔር ተከታይ መሆን ነው
። ሰለዚህ ሀጢአታችንን ለመምህረ ንስሐችን ለመናዘዝ እንፋጠን ነገር ግን
አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ይመስገን ምንም አልሰራንም (ሀጢአት የለብንም)
አንዳንዶቹ ደግሞ ባለፈው ሳምንት ነው ቅዱስ ቁርባን የተቀበል ነው ይላሉ ነገር
ግን ለሰው በ3 ቀን ውስጥ ሀጢአት ሳይሰራ መኖር ይቻለዋልን? ሰለዚህ
የዲያቢሎስን እቅድና አላማ ልናስተውል ይገባል ።

ተተተ "ስለ ንስሐ ሊያውቁአቸው የሚገቡ አንኳር ጉዳዮች" ተተተ

★ንስሐ ከሚደገሙ የቤተክርስቲያን ምስጢራት አንዱ ነው ሰለዚህ ቢቻል ክአንድ
ወር እስከ አንድ ወር ተኩል በሆነ ጊዜ ውስጥ ልንፈፅም ይገባል ምክንያቱም
ለቸልተኝነት እንዳንጋለጥ።ሰለዚህ ነገር ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ " ደጋግመህ ሀጢአት
በተሰራ ደጋግመህ ንስሐ ግባ ቤተክርስቲያን ሐኪምቤት እንጂ ፍርድ ቤት አይደለችምና"
በማለት በህይወታችን ውስጥ ለአንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በድግግሞሽ የምንፈፅመው
ታላቅ ምስጢር እንደሆነ ይናገራል።

★ንስሐችንን በምንናገርበጊዜ ከልክ ያለፈ እፍረት አይገባም ምክንያቱም
ጠላታችን ይህንን ድካም ተጠቅሞ ሀጢአታችንን እንድንሰውር ስለሚያደርገን
ምንም እንኳን ማፈር ከባድ ስሜት ቢሆንም በሌላ በኩል ደግም ጥቅም አለው
።ይኸውም የሀጢአትን መጥፎነትና አሳፋሪነት እንድናስተውል ያደርጋል። ሀጢአትን
ስንሰራው እንደቱደሰትን ሁሉ በሠራነው ሀጢአት ማፈርና መደንገጥ ይጠቅመናል።
አባቶቻችንም "ሀጢአትን መናዘዝ ዳግመኛ እንዳትበድል ይረዳሀል "ያሉት ለዚህ
ነው። "ወዳጄ ሆይ! ማፈር የሚገባህ ኃጢአት ስትሰራ እንጂ ንስሐ ስትገባ አይደለም። ኃጢአት ሕመም ነው። ንስሐ ደግሞ
መድኃኒቱ ነው። ከኃጢአት ቀጥሎ ህፍረት አለ ፤ ከንስሐ ቀጥሎ ግን በጌታ የኾነ ደስታ አለ። ነገር ግን ሰይጣን ይህን ቅደም
ተከተል አዛብቶብን በኃጢአት ስንደሰት በንስሐም እናፍራለን። "(ቅ.ዮሀንስ አፈወርቅ)

★ሁሉንም አይነት ሀጢአት (በማሰብ ፣በመናገር ፣በማድረግ የሰራኸውን)

በጥልቀት ተናዘዝ ያማለት ስንት ጊዜ ፣ ከማንጋ ፣ እንዴት እንደፈጸምከው ተናዘዝ ።
አንድ ምእመን ንስሃ በሚገባበት ጊዜ ሃጢያቱን ሳያድበሰብስ በዝርዝር ለካህኑ
በሚገባ መልኩ መናዘዝ አለበት ። እንዳው በደፈናው “እኔ ያልሰራሁት ሃጢያት
የለም ” ”አድርጉ ከተባለው ውስጥ ያደረግኩት አንድም መልካም ነገር የለም!”
እያሉ የብልጠት ኑዛዜ መናዘዝ አይገባም። አንድ በሽተኛ በሃኪም ፊት
”ታምሜአለሁ! ” ”በሽታ የተባለ ሁሉ አለብኝ!” በማለት መድሃኒት እንደማያገኝ
ሁሉ ሃጢያቱን በዝርዝር እና በግልፅ ያልተናገረም በትክክል ስርየት አያገኝም

★. አንድ ምእመን ስለ ሃጢያቱ በግልፅ ሊናገር እና ሊዘረዝር ይገባል ሲባል ግን
በሆነው ባልሆነው ”እኔ ሃጢያተኛ ነኝ” ሊል ይገባል ማለት አይደለም። ”ድሃ
ድህነቱን በአፉ ይጠላታል” ሲራ 13-24 እንዳለ ”እንደኔ ሃጢያተኛ ማን አለ?” እያሉ
ሃጢያትን በአፍ መጥላት ገና ከሀጢያት ፍቅር ያለመላቀቅ ምልክት ነው።ሃጢያትን
የሚጠላት በንስሃ ይርቃታልና። ሃጢያተኛ ነኝ እያሉ በማወጅ ንጹሃን ትሁታን
የሚመስላቸው አሉ። ትሁታን ግን ቅዱስ ዮሃንስ አፈወርቅ እንዳለው ሃጢያተኛ ነኝ
የሚሉት ሳይሆኑ ሃጢያተኛ ሲባሉ የሚታገሱት ናቸው።

★• በኑዛዜ ወቅት ትንኝን እያጠሩ ግመልን እንደመዋጥ ታላላቅ ሃጢያቶቻችንን ከጎን
ትተን ጥቃቅኑን ብቻ መናገር ስህተት ነው። ሲሰሩት ያልፈሩትን ሃጢያት ሲናገሩት
መፍራት አይገባምና። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በአርጋኖን ዘረቡዕ 7-5 እንዲህ
እንዳለ ”ሃጢያቴን ለመናገር ለምን አፍራለሁ? አለመናዘዜስ ለምንድን ነው? እኔ
ሀጢያቴን ብሰውረው ሃጢያቴ ራሱ ሊከሰኝ ይጮሃል። እንኪያስ እንዳልበደለ ለምን
ዝም እላለሁ? የሰራሁትን ክፉ ስራዬ ያሳጣኛል እኔ እንዳልሰራ ለምን እሆናለሁ?
የሚዘልፈኝ አልሻም፡ እኔ ራሴ ለራሴ የራሴን ዘለፋ አነባለሁ እንጂ”።

★• በኑዛዜ ወቅት ለሀጢያት ምክንያት መደርደርና የሌሎችን ሀጢያት አክሎ መናገር
አይገባም ”እገሌ እንዲህ አድርጎ ስለገፋፋኝ እንዲህ አድርጌ ነበር” አያሉ ሌላውን
መክሰስና ምክንያት መስጠት ይቅር ሳይሉ ይቅርታ መሻት ነውና። ጌታችንም
በወንጌል ”ከሳሾችሽ ወዴት አሉ?” ያላትን ሴት ”እኔም አልፈርድብሽም” ብሎ
በይቅርታ ያሰናበታት ስለ ከሳሾችዋ አንዳች ባለመናገሩዋ ነበር ዮሀ 8-11።

★• ሰው ሆኖ የማይበድል እንጨት ሆኖ የማይጨስ የለምና እንዲሉ ሰው ሁልጊዜ
ከበደል ንጹህ ይሆን ዘንድ አይችልም በንስሃ ሃጢያቱን የሚናዘዝ ሰው ዳግመኛ
አይበድልም ማለት አይደለም። ከንስሃ በሁዋላ በሃጢያት ተፈትነን ብንወድቅ
ተስ”ፋ ሳንቆርጥ ወዲያው ንስሃ ልንገባ ይገባል ”መልሼ ልበድል ለምን ንስሃ
እገባለሁ” ማለት ግን ”መልሶ ለሚርበኝ ለምን እበላለሁ” ”መልሼ ለምቆሽሽ
ለምን እታጠባለሁ” እንደ ማለት ነው ቅዱስ ዮሃንስ አፈወርቅ ”መውደቅ አዳማዊ
ነው ወድቆ አለመነሳት ግን ዲያቢሎሳዊ ነው” እንዳለው ተሰፋ ቆርጦ በንስሃ
መነሳት ይኖርብናል እግዚአብሄር ይቅር ማለት ሳይሰለቸዉ ሰው ይቅር በለኝ ማለት
ሊሰለቸው አይገባም

♥♥♥ " ከንስሀ በፊትና በኋላ ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄ" ♥♥♥

1 .ከንስሀ በፊት አንተ ሀጢአታቸውን ከሚረሱ ሰዎች ወገን ከሆንክ በአንድ ወረቀት ላይ ሀጢአቶችህን ፅፈህ እንዳይረሳህ
ብታስቀምጥ መልካም ነው።

2) ከንስሀ በፊትም ሆነ በኋላ አብዝተን ልንጸልይ ይገባል በተለይ መዝ6፣ መዝ 50
እና ፀሎተ ምናሴን ብንፀልይ መልካም ነው።

3. እራስህን መፈተን እና ከሀጢአት መንገዶች መሸሸ ይገባል ፦ የበለስ ቅጠል ሰፊና ደስ የምታሰኝ ናት፤ ወደ ጥፋት
የምትወስደው የኃጢአት መንገድም ሰፊ በር ናት። የበለስ ፍሬ ሲበሏትና ሲያላምጧት ጣፋጭ ናት፤ ኃጢአትም ሲሠሯት ደስ
ታሰኛለች። ከሠሯት በኋላ ግን (እንደ በለሲቱ) መከራን ታመጣለች። በሚሠሯት ጊዜ ጣፋጭ ከሠሯት በኋላ ግን መራር ናትና
እርሷን ከመሥራት መሸሸ ይገባል።
ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፀጥ ባለ ቦታ ብቻህን ተቀመጥና ራስህን ፈትን።
እግዚአብሔር ምንያክል ጸጋና በረከት እንዳተረፈረፈልህ አንተ ደግሞ ምንይህል
ጊዜ ሀጢአት በመስራት እንዳሳዘንከው አስብ ። ያንተን ህይወት ከቅዱሳን ህይወት
ጋር አነፃፅረው። ፃድቅ በጭንቅ የሚድን ከሆነ ሀጢአተኛ ወዴት ይታይ ዘንድ አለው
1ጴጥ4፥18 የሚለውን ቃል አስተውል? በተደጋጋሚ ለኃጢአት የሚገፋፉ ኹኔታዎችን፣ ቦታዎችን ወይም ጓደኛን በአጠቃላይ
እንደየኃጢአቱ መነሻነት መራቅ ያስፈልጋል። “ከንጹህ ጋር ንጹህ ኾነህ ትገኛለህ፤ ከጠማማም ጋር ጠማማ ኾነህ ትገኛለህ”
ይላል ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት /መዝ.18:26/። ቅዱስ ጳውሎስም፦ “እትሳቱ፤ ክፉ ባለንጀርነት መልካሙን አመል
ያጠፋል” ይላል /1ኛ ቆሮ.15:33/። በዚህ መሠረት ኹላችንም ኃጢአትን ደጋግመን የምንሠራው በኹኔታዎች ተጽዕኖ ነው?
በጓደኞች ግፊት ነው? ወይስ በምንሰማው፣ በምናየው፣ በምንዳሰሰው ተጽዕኖ? ይህን በአግባቡ ከለየን በኋላ ከምንጩ
ለማድረቅ ለዚያ ከሚዳርጉ ኹኔታዎች መሸሸ ተገቢ ነው። ይህን ስናደርግም ከምንም በፊት ሕሊናን ማሳመን ይጠይቃል።
በመቀጠልም አካላዊ ውሳኔ መስጠትን ነው። ለኃጢአት በሚዳርግ ቦታ ተቀምጠን “በፍጹም አይነካኝም፤ አይደርስብኝም”
ማለት መመጻደቅ ነው። ሰይጣንም እኛን ለመጣል አያርፍምና የምንወድቅበትንም መንገድ ያዘጋጃልና በሕሊናም በአካልም
ከዚያ መሸሸ ያስፈልጋል። የጴጥፋራ ሚስት ዮሴፍን ለክፉ ሥራ ስትከጅለው ቆሞ አልተሟገተም፤ ጥሏት ሸሸ እንጂ /ዘፍ.39/።
ስለዚህ ለተደጋጋሚ ኃጢአት ከሚዳርጉንና ከሚገፋፉን ነገሮች “እችለዋለሁ፤ እቋቋሟዋለሁ” ብሎ መመጻደቅ ሳይኾን መሸሸ
ካለብን መሸሸ ያስፈልጋል። እንደየኹኔታው በይበልጥም ከክፉ ቦታዎች፣ እንደየኃጢአቱ መነሻነት መሸሸ ያስፈልጋል።

4) ኃጢአቱ በሥጋም በነፍስም ጎጂ እንደኾነ ማስተዋል።
ይህ በተመሳሳይ እየወደቅንበት ያለው ኃጢአት በሥጋም ጭምር የሚጎዳን ይኾናል። ከክርስትና ሕይወት ባሻገር ስብእናን የሚያጎድፍ፣ ጤናን የሚያውክ ሊኾን ይችላል። ከዚህ አንጻር የዚህ ጉዳት በጥልቀት ማስተዋል ያስፈልጋል፤ ጉዳት ማሰብ ለመጠንቀቅ ይረዳልና።

5.ከንስሃ (ከኑዛዜ) በኋላ እግዚአብሔር ምን ውለታ እንደዋለልህ በመንፈሳዊ
እንቅስቃሴህም ምን ያክል ደስተኛ መሆን እንዳለብህ እያሰብክ ለብቻህ መሄድን
ብትመርጥ የተሻለ ነው። በብዙ ሰዎች ዘንድ የሚዘወተረው ስህተት ይህ ነው
ለኑዛዜ በሚሄዱበት ጊዜ በአንድነት ይሄዳሉ ከኑዛዜ በፊት ያለውን ጊዜአቸውን
በቀልድና በማይረቡ ውይይቶች ያባክኗቸዋል ስለሰሩት ምንም አያስቡም የሀዘንና
የመፀፀት ስሜት አይነበብባቸውም። ተናዘው ካበቁ በኋላ ቀድሞ ሲወያዩበት
እንደነበረው ያለ የማይረባ ንግግርን በመነጋገር ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። በዚህ
አይነት በወርቅ የተመሰለውን የእውነተኛ ኑዛዜ ጊዜያቸውን ስለሚያጠፉ በፀጥታ
ከራሳቸውጋር የሚሆኑበት ጊዜ አይኖራቸውም።

6) ከመምህረ ንስሐና ከሌሎች መምህራን እንዲኹም ከመንፈሳዊ መጻሕፍት ትምህርትን በመቅሰም የቅዱሳንንም ገድል በማንበብ ለቀጣዩ ገድል መዘጋጀት ፦
መንፈሳዊ እድገት የሚመጣው ደርጃ በደረጃ እንጂ በአንድ ጀምበርም የሚመጣ ለውጥ ስላልሆነ በሒደት ሀጢያትን ለመተው ፈጽመንም ለመራቅ በፅድቅም ለመበርታት በራሳችን ጉልበት ብቻ ስለማንችል "ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም" ብሎናልና /ዮሐ.15፡5/። በዚህም መሠረት ከመምህራን የምንሰማው የእግዚአብሔር ቃል፣ ከመጻሕፍት የምናገኘው፣ ከመምህረ ንስሐም በጸሎትና በምክር የምናገኘው ተግሳፅ ያ እያጠቃንና እየጣለን ያለውን ከይሲ እንድናሸንፍበት ኃይል ይኾነናል።

7) መንፈሳዊ ተግባራትን ማዘውተር።
እንግዲህ እንደየ ክስተቱ ለየትኛውም የኃጢአት ተግባር መንፈሳዊ ሕይወት፣ መንፈሳዊ ተግባር ድል መንሻው ነው። ይህም "እንዲህ ያለውን ክፉ መንፈስ ያለ ጾም ያለ ጸሎት ከእናንተ አይወጣም" እንዳለ /ማር.9፡29/ ጾምን፣ ጸሎትን፣ ንስሐን የሕይወታችን መሠረት ማድረግ ተገቢ ነው።

8) የመጨረሻውና ዋነኛው ከንስሀ በኋላ ቅዱስ ቁርባንን መቀበል ነው። የጠፋውን ልጅታሪክ ስንመለከት
ከጠፋበት ሲመለስ ቀድሞ ያየው አባቱ ነው ነገር ግን ቶሎ ወደቤት አላስገባውም
ባሮች በተባሉ ካናት ንፅህናው እንዲመለስለት አዲሱን እንዲደርቡለት አደረገ እንጂ ከዛም የሰባ ፍሪዳ
የተባለ ክብር ይግባውና መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው "የሰባውን ፊሪዳ
አምጥታችሁ እረዱት፥ እንብላም ደስም ይበለን፤"(ሉቃ15:11-23) አለ በሰማይ
በአባታችን ዘንድ ታላቅ ደስታ የሚሆነው በመመለሳችን(በንስሀችን ብቻ አይደለም)
ቅዱስ ስጋውን ክቡር ደሙን በመብላታችን ጭምር ነው።እኛም በክርስቶስ ኢየሱስ
አዲስ ፍጥረት ለሆንን እና ኩነኔአችን ለቀረልን
ለእኛ.....
ዘፈን.....አይገባም!
ስካር.....አይገባም!
ዝሙት.....አይገባም!
ሴሰኝነት.....አይገባም!
መዳራት.....አይገባም!
ባዕድ አምልኮ.....አይገባም!
እርኩሰት.....አይገባም!
ክፋት.....አይገባም!
ምቀኝነት.....አይገባም!
ሀጢአት.....አይገባም!
ተንኮል.....አይገባም
ምንፍቅናም.....አይገባም!
ቁጣና ቂም.....አይገባም! ስለቂምና ስለ ቁጣ (ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ)ዘርዘር አድርጎ ሲመክር እንዲህ ይላል
"በባልንጀራህ ላይ የምትቆጣ ከሆነ የአንተ ቁጣ በእግዚአብሔር ላይ ነው። በባልንጀራህ ላይ ቂምን በልብህ የያዝክ ከሆነ
ቂምህ በጌታ ላይ ነው። ባልንጀራህን በከንቱ የምትቆጣው ከሆነ ኃጢአት በአንተ ላይ ይስለጠንብሃል። ልብህን የፍቅር ማደሪያ
ካደረከው በምድር ላይ አንዳች ጠላት አይኖርህም።"
"እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ በጎ እንደሆነ የሚጣልም እንደሌለበት
እንናገራለን።(ቅዳሴ) እንደሚል ዘረኝነት የሚሉትም ቆሻሻ አስተሳሰብ ለክርስቲያን በፍፁም አይገባም ነውር ነው ስራውን ስንንቅ
ስንሰድብ የሰራውን (እግዚአብሔርን) መሳደብ ነው!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!! የክርስቲያን ብልጫውም
ሁሉን መውደዱ ስለሆነ ። "ልባችንን ጠፊና በስባሽ ከኾነው ከምድራዊው ምኞት አርቀን ከበደል በንስሐ ነጹሕ ካደረግነው በጸጋ
መንፈስቅዱስ የተሞላን እንሆናለን።"(አባ ኢብርሃም መፍቀሬ ነዳያን)
ስለዚህ እነዚህን የመሰሉትን የሀጥያት ስሮች ቆርጠን ጥለን
ፍቅሩን አያሰብን በጨመረልን ዘመን ንስሀ ገብተን ስለሀጢአታችን የተሰጠውን
ቅዱስ ስጋውን በልተን ክቡር ደሙን ጠጥተን እንድንድን እግዚአብሔር ይርዳን አሜን።
" በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በእናንተ እያደረገ፥ ፈቃዱን
ታደርጉ ዘንድ በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹማን ያድርጋችሁ፤ ለእርሱ እስከ ዘላለም
ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።"(ዕብ13:21)
ስለንስሀ ይህን ያክል ከተነጋገርን በቀጣይ
ደግሞ የሚስጢራት ሁሉ እራስ ሰለሆነው ስለ ቅዱስ ቁርባን እንነጋገራለን
።

☞ተተ ቅዱስ ቁርባን ተተ☜

☞ **ምስጢረ ቁርባን:-** ቁርባን የሚለው ቃል የሱርስት ቃል ሲሆን
ትርጉሙ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መንፈሳዊ አምኃ፣ መስዋዕት ፤ መባዕ
ለአምላክ የሚቀርብ የሚሰጥ መንፈሳዊ ነገር ሁሉ ማለት ነው። ቅዱስ ቁርባን ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዱ ምስጢረ ቁርባን ሲሆን
: ቅዱስ ቁርባን በሚከወንበት ስርአትና በሚያስገኘው ጥቅም በሁለት ከፍለን እናየዋለን።
1/•ቁርባን በብሉይ ኪዳን :-የብሉይ ኪዳኑ ቁርባን ከሰው ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ነበር በዛ ዘመን ይቀርብ የነበረው የመስዋዕትም(ቁርባን) ከበግ ፤ ከላምና ከተለያዩ እንስሳት የተዘጋጀ ነበር። እንደምሳሌ ብናይ " ለማስተስረያም እንዲሆን ደማቸው ወደ መቅደስ የገባውን የኃጢአቱን መስዋዕት ወይፈንና የኃጢአቱን መስዋዕት ፍየል ከሰፈሩ ወደ ውጭ ያወጡአቸዋል፤ ቁርበታቸውንም፥ ሥጋቸውንም፥ ፈርሳቸውንም በእሳት ያቃጥላሉ።"
(ኦሪት ዘሌዋውያን 16:27) ይላል በተጨማሪም (ዘሌ 4÷24) ማንበብ አንችላለን።

2/• ቅዱስ ቁርባን በሀሐዲስ ኪዳን :-የሐዲስ ኪዳኑ ቁርባን ግን ፍፁም ልዮ ነው ከሶስቱ አካል አንዱ ወልደ እግዚአብሔር ወልደ ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች አንዴ ባቀረበው መስዋእት ለዘላለም ድነናል።
" በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል።ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል፤ እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ። "(ዕብ10÷10~12) ያማለት ግን ከውርስ ሀጢአታችን አነፃን ጥንተ አብሶን አስቀረልን ለማለት ነው እንጂ ዛሬም በድካማችን ምክንያን ስናውቅ በድፍረት ሳናውቅ በስህተት ለምንሰራው ሀጢአት ሁሉ ስርዬት አግኝተናል ለማለት አይደለም እውነት ነው አዳምና ሔዋን ካመጡት እርግማን ተፈተናል ነገር ግን እኛ የበደልነውን በንስሀ አወራርደን ከዚህ ቅዱስ መአድ መሳተፍ ግድ ይላል። የብሉይ ኪዳኑ ቁርባን ስጋዊ ምህረትንና በረከትን ያመጣ ነበር እንጂ ነፍስን አያድንም ነበር ነገር ግን በሐዲስ ኪዳን የሚደረገው መስዋዕት ፍፁም በረከትን ፣ምህረትን ፣ ይቅርታን ፣ፈውስንና መባረክን በስጋና በነፍስ ላይ የሚያመጣ ከእግዚአብሔር ወደ ሰው የተሰጠ ስለሆነም ቅዱስ ቁርባን እንለዋለን እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና።

•••በብሉይ ኪዳን መስዋዕት{ ቁርባን } በረከት ያገኙ አባቶች•••

- አዳም አባታችን ባቀረበው መስዋዕት ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ ሰው ሆኖ እንደሚያድነው ቃል ገባለት ፣ ዘፍ 3 ፥ 22 ፣ ገላ 4 ፥ 4
- ኖኅ ባቀረበው መስዋዕት ለኖኅና ለልጆቹ ምድርን ዳግም በመቀሰፍት እንደማያጠፋት በቀስተ ደመና ምልክት ቃል ገባላቸው ዘፍ 9 ፥ 1 ፣ ዘፍ 9 ፥ 8

- አብርሐም አባታችን ዘፍ 18 ፥3 አባታችን አብርሐም ባቀረበው መስዋዕት በዘርህ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ የሚለውን የተስፋ ቃል ሰማ ያም ዘር የተባለው ለጊዜው ይስሐቅ ይሁን እንጂ ፍጻሜው ግን ሊመጣ ላለው ለክርስቶስ ነበር ።
- መልከ ጼዴቅ ዘፍ 14 ፥ 17 ፣ መዝ 109 ፥ 4 ፣ ዕብ 5 ፥ 6 በእግዚአብሔር ፊት ባቀረበው መስዋዕት ክህነቱ ለዘለዓለም ተብሎለት የክርስቶስ ምሳሌ ሆነ ዕብ 7 ፥ 1
- ዳዊት መዝ 131 ፥ 11 መስዋዕት ባቀረበበት ሠዓት ከአብራክህ የተገኘው ልጅህ በዙፋንህ ይነግሣል ተባለለት ይህም ለጊዜው የተነገረው ለሰሎሞን ቢሆንም ፍጻሜው ለክርስቶስ ነበር መዝ 71 ፡1 ሌሎችም በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ መስዋዕታቸውን እያቀረቡ በረከት ተቀብለዋል ። በሐዲስ ኪዳን ግን እንስሳት በቤተ መቅደስ ውስጥ መስዋዕት (ቁርባን) ሆነው አይቀርቡም፤ መስዋዕት ሁሉ በክርስቶስ ሥጋና ደም ተጠቃሏልና ።
ይህንም የአዲስ ኪዳን መስዋዕት የመሠረተው ራሱ ጌታችን ሲሆን ፤ በጸሎተ ሐሙስ ማታ አስራ ሁለቱ ሐዋርያት እንዳሉ በመጀመሪያ መስዋዕተ ኦሪትን ሰርቶ ካሳለፈ በኋላ ኅብስቱና ወይኑን ባርኮ “ነገ በመስቀል ላይ የሚቆረሰው ሥጋዬና የሚፈሰው ደሜ ይህ ነው ብሉ ጠጡ ብሎ ሰጣቸው” ማቴ 26 ፥ 26 ።
በመሆኑም ማንኛውም በክርስቶስ ክርስቲያን በወልድ ውስደ እግዚአብሔር፣ በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ የተባለዉሆነ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይሔማኝ ዘላለማዊ ህይወትን ለማግኘት የጌታችን የፈጣሪያችን የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ስጋና ደም የመቀበል ሐይማኖታዊ ግዴታ አለበት ‹‹በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው›› እንዲል ክርስቶስ።
ምስጢረ ቁርባን ካህኑ ኅብስቱን በጸህል ወይኑን በጽዋ አድርጎ በጸሎተ ቅዳሴ እየጸለየ በባረከው ጊዜ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኮት ይሆናል ። አንዳንዶች እንደሚመስላቸው ይህ ቅዱስ ቁርባን አማላጅ አይደለም አማናዊና ፈራጅ ነው እንጂ " ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና።" (1 ቆሮ 11:29)
እኛም ይህን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም በምንቀበልበት ጊዜ ለእኛ ሲል የተቀበለውን መከራና ስቃይ እናስባለን የክርስቶስን ሥጋውንና ደሙን የምናገኝበት ቦታ በቤተ መቅደስ ብቻ ነው። የሚያገኘውም በኅብስትና በወይን መልክ ነው። በኅብስትና በወይን መልኩ መገኘቱም እንዲህ ነው። በቤተ መቅደስ ውስጥ መንበረ ታቦት አለ፣ ታቦቱ በመንበሩ ላይ ይኖራል። ጸሎተ ቅዳሴ በሚደረግበት ጊዜ ቄሱ (ቀዳሹ ቄስ) ኅብስት በጸህል፣ ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ በታቦቱ ላይ ለእግዚአብሔር ያቀርበዋል፤ እግዚአብሔር እንዲባርከው እንዲቀድሰው በታቦቱ ላይ ያቀርብና “አሐዱ አብ ቅዱስ፣ አሐዱ ወልደ ቅዱስ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ”ብሎ ሃይማኖትን ይመሰክራል። ሕዝቡም (ምእመናኑም)የቀሲሱን ቃል ተከትለው “በአማን አብ ቅዱስ፣ በአማን ወልደ ቅዱስ፣ በአማን ውእቱ መንፈስ ቅዱስ” ብለዉ ሃይማኖት ይመሰክሩበታል። ከዚህ አያይዞ ሙሉ ጸሎተ ቅዳሴ ይደርስበታል (ይጸለይበታል)።

በጸሎተ ቅዳሴው ውስጥ ቡራኬ የሚደረግበት ጸሎት አለ፣ ቄሱ እንደ ሥርዓቱ እየጸለየ በኅብስትና በወይኑ ላይ ቡራኬ ያደርጋል፣ ጸሎተ ቅዳሴውንም ሲጸልይ “አቤቱ ወደዚህ ኅብስትና ወደዚህ ወይን መንፈስ ቅዱስንና ኃይልን እንድትልክ እንለምንኃለን፣ የጌታችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውንና ደሙን ያደርገው ዘንድ” የሚለዉን ጸሎት እየጸለየ ቀዳሹ ሕብስቱንና

ወይኑን ይባርካል፣ ይህን ጊዜ (ይህን የሚጸለይበት ጊዜ) በመንፈስ ቅዱስ ኃይል (በመንፈስ ቅዱስ ሥራ)ኅብስቱ የክርስቶስ ሥጋ፣ ወይኑ የክርስቶስ ደም ይሆናል። ይህም ጸሎት ይረስዮ ይባላል። የሚገኘውም በቅዳሴ ሐዋርያትና በቅዳሴ እግዚእ ነው በሌሎቹ ቅዳሴዎችም ይህን የመሰለ ጸሎት አለ፣ ከዚህ ቀጥሎ እያይዞ ቄሱ እየመራ፣ ሕዝቡ እየተከተለ “ሀበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ ወፈውሰነ በዝንቱ ጽርስፎራ...” እያሉ ይጸልዩበታል።ቀጥሎ ጸሎተ ፈትቶ (እየቄረሱ የሚጸለይ) አለ፣ ቄሱ ያን እየጸለየ እንደ ሥርዓቱ ሥጋውን ይቄርሰዋል። ፍታቴውን ሲፈጽም ቄሱ እየመራ ሕዝቡ እየተቀበሉ አርባ አንድ ጊዜ እግዚአታ (እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ) ያደርሱበታል። ቀጥሎ ቄሱ “አአምን፣ አአምን፣ አአምን፣ ወእትአመን ...እያለ ሥጋውን በደሙ”“ ብሩክ እግዚአብሔር አብ አሀዜ ኩሉ ዓለም አምላክነ ወብሩክ ወልድ ዋህድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ ወብሩክ መንፈስ ቅዱስ ጸራቅሊጦስ መጽንዒ ወመንስዔ ኩልነ...”እያለ ደሙን በሥጋው ሦስት፣ ሦስት፣ ጊዜ ይባርከዋል። ከዚህ በኋላ በቅድሚያ ቀዳሾች ካህናት፣ ቀጥሎ ሕዝቡ በቄሱ እጅ እንቄርባለን (እንቀበለዋለን)።
ስንቀበል ሰውነታችንን ከኃጢአት ንጹህ አድርገን በንስሓ የቀረውን በደላችንን እንደሚደመስስልን ፤ከበደል እንደሚያነጻንና የዘለዓለም ሕይወት እንደሚሰጠን አምነን መሆን አለበት ።
ቅድስ ቁርባን የሚስጥራት ሁሉ ማህተም (እራስ) ነው ክርስትና (ምስጢረ
ጥምቀት)፣ ምስጢረ ጋብቻ ፣ምስጢረ ክህነት የሚታተመው በቅዱስ ቁርባን ነው።
እውንነው ለኪዳን እንፈጥናለን ቅዳሴን አናስታጉልም በእርግጥም የቃሉ ሙላት አለን ደግሞም ለቅዱስ ቁርባን ክብር አለን ለነፍሳችን መድሀኒትነቱን ማንም
እንደማይተካከለው እናውቃለን ግን መቼ ነው ወደዚህ ቅዱስ ማእድ የምንቀርበው?
እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል ት.ኤር 2፥32 "ህዝቤ ግን ለማይቆጠር ግዜ
እረስቶኛል" ይላል ቅዱስ ቁርባን መቀበል ካቆምን ስንት ጊዜ ሆነን? ሰለሆነም ይህ
የአምላካችን ልምምጥ ሊገባን ይገባል።

•••ቅዱስ ቁርባን መቀበል የሚገባን ለምንድን ነው?•••

(1)• ስርየተ ሀጥያት ለማግኘት ነው፦ ማቴ 26፥28 ህብስቱን አንስቶ ባረከ ቀደሰ (አመሰገነ) ከዛ ስለ ብዙዎች ለሀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው የምናየው አካለ ህብስት ነው የምናምነው ግን አማናዊው የክርስቶስ ቅዱስ ስጋ ብለን ነው። የምናየው አካለ ወይን ነው ስላልበቃን የምናምነው ግን አማናዊ የክርስቶስ ቅዱስ ደም ብለን ነው ። (ቅዱስ ዮሀንስ አፈወርቅ)እንዳለ ."የምናየው የምናምነውን አይደለም የምናምነውም የምናየውን አይደለም" ስላልበቃን ነው እንጂ ለበቁ አባቶች ቀራንዮ እንደታረደ ሆኖ ታይቷቸዋል። ነዋይ ህሩይ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለ " .....በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር....."(ገላ 3:1) ሰለዚህ ስናውቅ በድፍረት ሳናውቅ በስህተት ለሰራነው ሀጢአት ፍፁም ይቅርታ የምንቀበልበት
የህይወት ማእድ ነው። እኛ ግን ለምን አትቆርቡም ስንባል ሀጢአተኛ ነኝ ነው የምንለው ነገርግን ማንም ሰው በቅቶ ስጋ ወደሙን መቀበል አይችልም ለመብቃት ይቀበላል እንጂ አንዳንድ ሰዎች የምንቆርበው እራሳችንን ከሀጢአት ካነፃን በኋላ (ፍፁም ከሆንን በኋላ) ያንን ንፅህና ለማረጋገጥ ሲባል እንደሆነ የሚመስላቸው ብዙዎች ናቸው። ይህ ስህተት ነው ነገር ግን የምንቆርበው ከሀጢአት ለመንፃትና በጎ ፍሬ ለማፍራት ነው። መድሀኒት ስለሆነም እንቀበለዋለን ሀኪም መድሀኒት የሚሰጠው ለታወቀ በሽታ ነው ለጤነኛ ግን የሚሰጠው ክትባት ነው። እኛደሞ በሀጢአት በሽታ ክፋኛ ታመናል ሰለዚህ እውነተኛውን የነፍስ መድሃኒት ቅዱስ ስጋውን ክቡር ደሙን ለሀጢአት ስርየት ልንቀበል ይገባል። ሀጥያት አለብን ወይስ የለብንም? " ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም"1ዮሀ 1፥8 ። ታድያ ለምን ንስሐ እየገባን አንቆርብም? "ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያነፃሀነ እምኩሉ ሀጣውኢነ 1ዮሀ1፥7-8 " እንደሚል ለመንፃት ለመፅናት ንስሀ እየገባን ቅዱስ ቁርባንን ልንቀበል ይገባል።

(2)• መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ካስገኘው ድል ተካፋይ
እንድንሆን ልንቀበል ይገባል ። መሀኒታችን በመስቀል ላይ ያስገኘልን ፀጋዎች
❖ ሀጢአትን ድል መንሳትን
❖ ሞትን ድል መንሳትን
❖ ጠላት ዲያቢሎስን ድል መንሳትን ቅዱስ ቁርባን በምንቀበልበት ጊዜ እነዚህን
ሁሉ ድል መንሳትን ይሰጠናል። ዲያቢሎስ ሰውን ድል ያረገው በምግብ ሰለሆነ
በመብል ምክንያት የመጣውን ሀጥያት በመብል ድል እንዲያደርገው ቅዱስ
ስጋውን ክቡር ደሙን ሰጠን እግዚአብሔር ከፈጠራቸው በየክፍል በየክፍሉ ቆጥረን
ከ22ቱ ፍጥረታ እንደሰው ያከበረው ያፈቀረው ማንም የለም ነገር ግን እንደሰው
ደግሞ ያስቸገረው ማንም ፍጡር የለም አትብሉ የሞት ሞት ትሞታላችሁ ስንባል
ተሸቀዳድመን በላን ስጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ የዘለአለም ህይወት ታገኛላችሁ
ስንባል ደግሞ እምቢ አንበላም አስቸጋሪዎች እኮነን ።
ነገርግን በቅዳሴ ፀሎት ላይ ካህኑ ቅዳሴ ከመግባታቸው በፊ እውስጥ
የሚፀልየው ፀሎት ውስጥ እንዲህ ይላል "በሰርጉ በአል ደስታ ቀን ለእድምተኞቹ
የእራሱን ስጋ የጋበዘ ሙሽራ ከክርስቶስ በቀር ማን ያየ አለ" ይላል ። እውነት ነው ማንም የለም ስለዚህ ከዚህ ድግስ ልንሳተፍ ይገባል።

(3) •በመንፈሳዊ ህይወት ለማደግ ፣ለመጎልመስና ለመጠንከር ቅዱስ ቁርባንን
መቀበል ይባገል፦
{ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ} የተባለው አባትም ስለ ቅዱስ
ቁርባን ሲያስተምር እንዲህ ነው ያለን “ወዳጄ ሆይ! የትዕቢት መርዝ ተጠራቅሞ
አብጦብኻልን? እንኪያስ ወደ ቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙ ቀረብ፤ ስለ ወዳጆቹ ሲል
እርአያ ገብርን የነሣ ትሑቱ ጌታም ትሕትናን ያስተምርኻል። የስግብግብነት ትኩሳት
አስቸግሮኻልን? ወደ ቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙ ቀረብ፤ ደግነትንም ትማራለኽ።
የምቀኝነት ብርድ አስቸግሮኻልን? እንኪያስ ወደ ሰማያዊው መዓድ ቀረብ፤ ምኅረት
ማድረግንም ገንዘብ ታደርጋለኽ። ትዕግሥትን የማጣት እከክ ይዞኻልን? እንኪያስ
ወደ ቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙ ቀረብ፤ ራስን መግዛትንም ገንዘብ ታደርጋለኽ።
በመንፈሳዊ ሕይወትኽ ልል ዘሊል ብትኾን ይኽን መንፈሳዊ መዓድ ተመገብና

ብርቱ ትኾናለኽ። ቆሸሸኻልን? እንኪያስ ወደዚኹ መብልና መጠጥ ቅረብ ብዬ
እመክርካለኹ፤ ንጽሕናንም ገንዘብ ታደርጋለኽ።" ነው ያለን ደግሞም ቅዱስ
ቁርባን የነፍስ ምግብ ነው ዮሀ 6፥55 እለዳለን በስጋ ከእናታችን እንደተውለድን
ሁሉ በጥምቀትም ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ በ40ና በ80 ቀን ስለተወለድን
ለስጋችን እድገት ምግብ እንደሚያስፈልግ ሁሉ ለነፍስም እድገትና ጥንካሬ ፀሎት፣
ቅዳሴ ፣ቃለ እግዚአብሔር ከሁሉ በላይግን ቅዱስ ቁርባን አስፈላጊዋነው በምግብ
ያልጠነከረ (የተጎዳ ሰውነት) በቀላሉ በበሽታ እንደሚጠቃ ሁሉ ከቅዱስ ቁርባንም
የራቀ ሰው የሀጢአት መመላለሻ መሆኑ የማይቀርነው። በአቡነ ዘበሰማያ ፀሎታችን ላይ ያለውን ፀሎት ስንቶቻችን
እናስተውላለን የእለት እንጀራ ስጠን እንላለን ነገር ግን የስጋውን ብቻ አይደለም ለነፍሳችንም ቅዱስ ስጋህንና ክቡር ደምህን
ስጠን ማለታችን ነው ። ነገር ግን ስላላስተዋነው ነፍሳችንን በረሃብ እየጎዳናት ነው።

(4)• ክርስቶስን የለበስን ፣ክርስቶስን በልባችን ያነገስን፣ ክርስቶስ የተዋሀደን
እንድንሆን ነው ቅዱስ ቁርባንን የምንቀበለው ዮሀ6፥56" ስጋዬን የሚበላ ደሜን
የሚጠጣ እኔም በእርሱ እርሱም በእኔ ይኖራል እንዳለ" ደግሞም ራእ 3፥20 ላይ እንደምናገኘው ከእኛጋር እንዲሆን እራትን
ከእርሱ ጋር ልንበላ ይገባናል።
(ቅዱስ አውግስጢኖስም)"አምላኬ ሆይ ምናልባት እኔ ሀጢአትን የህይወት ምንጭ
አድርጌ ከሀጥያት ጋር ተጣብቄ ስኖር እኔ ከአንተ ጋር ያልነበርኩበት ጊዜ ቢኖር
እንጂ አንተ ግን ከእኔ ጋር ያልነበርክበት ጊዜ በህይወቴ ወስጥ የለም" ነው ያለው።
ስለዚህ ተመልሰን በአባትነት ፍቅሩ እየተጎበኘን መኖር ይሻለናልና ቅዱስ ቁርባንን እንቀበል።

(5)• በመስቀል ላይ የፈፀመልንን የአድህኖ ስራ እናስታውስበታለን ፦መምህራን
"የሀጢአት ትልቁ ክፋ መስራት ሳይሆን የክርስቶስን ውለታ መርሳት ነው" ይላሉ።
(አረጋዊ መንፈሳዊ) "ፈውስ ህማማቲየ በህማማቲከ" ማህየዊ የሆንክ ጌታ ሆይ
ስለኔ በቆሰልከው በቁስልህ የነፍሴን የሀጢአት ቁስሏን ፈውስላት ይላል።
ደግሞም በቅዳሴያችን ላይ ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ..... አቤቱ አምላክ ሆይ ሞትህን
እናስባለን ቅድስት ትንሣኤህን እንነግራለን ዕርገትህንና ዳግመኛም መምጣትህን
እና።ምናለን እናመሰግንሃለን እናምናለንም ጌታችንና አምላካችን ሆይ እንለምንሃለን
እንማልድሃለንም። የምንለው በከንቱ አይደለም በበላን በጠጣን ጊዜ እንድናስብ
ስላዘዘ ነው ደግሞም ውለታውን ይህች ቤተ ክርስቲያን ስለማትረሳም ነው።
መምህንራ ስጋ ወደሙ ለምን በመብልና በመጠጥ ሰጠን ሲሉ 3 መሰረታዊ
ነገር ተገልፆላቸዋል።

1/ መብልና መጠጥ ያፋቅራል፤ ቅዱስ ስጋውና ደሙም የክርስቶስን ፍቅር በልቦና
ያሳድራልና አንድም እወዳችኋለሁ ሲለን ነው ።
ምግብ ለሥጋችን ኃይል እንደሚለግሰን። ሥጋውና ደሙም ለነፍሳችን መንፈሳዊ
ኃይል እንዲሰጠን ። የተራበና የተጠማ ሰው ብር፣ ወርቅ ከሚሰጡት ይልቅ
መብልና መጠጥ የሰጠውን እንደሚወድ ጌታም ፍቅሩን ሲገልጥልን ነፍስ
ርሃባችንን ሊያስወግድ እንዲህ አደረገ

2/ ለካሳ፦ በመብል የጠፋው አለም በመብል እንዲድን፤ አዳምና ሄዋን በምግብ
የእግዚአብሔር ልጅነታቸውን እንዳስወሰዱ ፤ በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ
ልጅነታችንን መለሰልን ። ዘፍ 3 ፥ 1 ፣ ዮሐ 6 ፥ 49 ።

3/ ለሰው የቱንም ያህል ብርና ወርቅ ቢሰጡት በአፍአ ነው እንጂ ከውስጥ ህይወት
ጋር አይዋሃድም ነገር ግን እሱ በስጋውና በደሙ ይዋሀደን ዘንድ ሰጠን ሰለዚህ
ገላ5፥1 ላይ በነፃነት እንድንኖር ክርስቶስ ነፃ አወጣን እንደሚል እስራኤላውያን
ከግብፅ ምድር ከመውጣታቸው በፊት በ10 ኛው መቅሰፍት ሞተ በኩር ጊዜ እነሱ ማለትም እስራኤላውያን የጠቦት በግ አርደው
ፋሲካን አድርገው ደሙን በበራቸው መቃን ቀብትው ስጋውን እየተመገቡ ከቀሳፊው መልእክ እንደዳኑ መፅሀፍ ይነግረናል
ዘፀ12፥7። እኛ ክርስቲያኖች በግብፅ ከተመሰለችው ከሲኦል ግዞት በፈርኦን ከተመሰለው ከዲያቢሎስ ግዞት ያመለጥ ነው
በበጉ በክርስቶስ ቅዱስ ስጋ እና ክቡር ደም ነው።
ቅ.ጳውሎስ በ" 1ቆሮ5፥7 ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶልናል" ሲል አስተምሮናል ታዲያ ከዚህ መአድ ከመሳተፍ የከለከለን ምንድን
ነው። አንዳንዶች ሲጠየቁ ለሽማግሌዎችና ለህፃናት ነው ብለው የሚያስቡ አሉ ነገር ግን ቅዱስ ቁርባን የጡረታ አበል አይደለም
እግዚአብሔርም የሚፈልገው የወጣትነታችንን ዘመን ሮጠን የማንጠግብበትን ለሁሉ ደረስኩ ደረስኩ የሚለውን የወጣትነት
ዘመን እንጂ ሽማግሌውማ አይኑ ሲፈዝ ጉልበቱ ሲደነግዝ እድሜው በራሱ ያስገዛዋል እንደ ዘመኑ ሽማግሌ" ሹገር
ዳዲ"እንደሚባሉት አይሁን እንጂ እነዚህ ደሞ ከልጆቻቸው ከልጅ ልጆቻቸው የሚሴስኑ የሽማግሌ ጎረምሶች ናቸው።
በእድሜያቸው አመሻሽ ላይ ሆነው እንኳን ወደ እግዚአብሔር የማይመለሱ ናቸው የፀሎት መፅሀፍ በመያዣቸው ሰአት
የብርጭቆ መጠጥ የሚጨብጡ ስጋቸውን ለእግዚአብሔር በማስገዣቸው ሰአት እነሱ ለዝሙት የተገዙ ብዙ ብዙ ታዲያ
በሽምግልና እንዲህ ከሆነ ሽማግሌ ስሆን ነው የምቀበለው እንዴት እንላለን ምንስ ዋስትና አለን ነገ ለመኖራችን " ወንድሞች
ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ" ገላ5:13 ነው የሚለን ሌላው ለምን
አትቆርቡም ስንባል አንዳንዱ አላገባሁም ፣ ተማሪ ነኝ ይላል፣የተመረቀው ስራ ልያዝና ይላል ፣ ስራ የያዘው ላግባና
ይላል....አንዳንዱ እነግዳለሁ፣ ሀጢአት ብሰራስ ገናነኝ(ወጣት ነኝ) ይላል
አስተውሉ ቅዱስ ቁርባን የጡረታ አበል አይደለም ሞት እንደ ሽማኔ መወርወሪያ
በፈጠነበት በዚህ ወቅት ነቅቶ መገኘት ተገቢነው ሰለሞን እንዳለ በጉብዝናችን
(በወጣትነት) ወራት ፈጣሪን ልናስብ ይገባል ።
ስለዚህ ስጋወ ደሙ ስንቀበል ሰለኛ የተቀበለውን መከራ እናስብበታለን ጌታችንም
ቅዱስ ቁርባንን ለሀዋርያት ሲያቀብል ሉቃ22፥19 ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት
ያለው የዚህ ቃል ሚስጢር ያልገባቸው ተረፈ አይሁድ መናፍቃን ቅዱስ ቁርባን
መታሰቢያ (ምሳሌ)ነው እንጂ አማናዊ አይደለም ይላሉ እግዚአብሔር ይቅር
ይበላቸው በዚሁ ክፍል ስናይ ባርኮ ፈትቶ ሲጨርስ ይህ ስጋዬና ደሜ ነው ነው
ያላቸው እንጂ የስጋና የደሜ ምሳሌ ነው አይደለም ያላቸው። ሌላም ለመታሰቢያዬ

አድርጉት ያለውን ቃል ጠቅሰው መታሰቢያ ነው ይላሉ ነገር ግን ከጎኑ "አድርጉት"
የሚል ቃል አለ ፍችው እናንተም ስሩት ማለት ነው ። ይህን ቃል በኦ.ዘፀ 12፥14
ካለው ጋር ስናስተያየው ህዝበ እስራኤል ከግብፅ ምድር የወጡበትን ፋሲካ አሁን
ድረስ ያከብራሉ ለምን? አ..ድ..ር..ጉ.. ስለተባለ። እና ታዲያ እኛ ሞታችንን የደመሰሰውን፣ የእዳ
ፅህፈታችንን የሰረዘውን ፣በመገረፉ ቁስል የፈወሰንን ከጽርስፎራው ስንበላና
ስንጠጣ ለኛ የከፈለውን ዋጋ እናስባለን ።

(6)• ፍሬ ሀይማኖት፣ፍሬ ምግባር ፣ፍሬ መንፈስ ቅዱስን አብዝተን ለማፍራት ነው።
የክርስቲያን ህይወት በተክል ይመሰላል። " ጻድቅ እንደ ዘንባባ ያፈራል፥ እንደ
ሊባኖስ ዝግባም ያድጋል።
በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተተክለዋል፥ በአምላካችንም አደባባይ ውስጥ
ይበቅላሉ።" (መዝ 92፥12-13)
ጌታም እዉነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ ነው ያለን እኛ ደሞ ቅርንጫፎቹ እንደሆንን
ነግሮ ከእርሱ ካልተጣበቅን ፍሬ እንደማናፈራ ፍሬም ከታጣብን ተቆርጠን ወደ
ዘላለም እሳት እንጣላለን ማቴ3፥8-12 ሰለዚህ ለንስሀ የሚገባ ፍሬን እንድናደርግ
እግዚአብሔር ያዘናል ትእግስቱም 2ጴጥ3፥5-8 ላይ እንደምናነበው እኛ ወደ ንስሀ
እንደርስ ዘንድ ነው።

(7)• ሌላው የዘላለማዊ ህይወት ለማግኘት ቅዱስ ቁርባን መቀበል ያስፈልጋል (ዮሀ6፥53-57) እውነት እውነት እላችኋለሁ
የወልደእጓለእመህያውን ስጋውን
ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ህይወት የላችሁም ነው ያለው
ሰለዚህ ቅዱስ ቁርባን የምንቀበለው ለዚህነው ከመቃብር አጠገብ ትንሳኤ ከሞት
በኋላ ሕይወት ከመሰደድ በኋላ መመለስ ስላለ የዛህ ህይወት ወራሶች ለመሆን ነው።

(8)• ፈፅመን ለመንፃትና ለመቀደስ ነው የምንቆርበው፦ እግዚአብሔር በባህሪው
ቅዱስ ነው ይህ ቅዱስ አምላክም እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ነው ያለን
ቅዱስ ቁርባንም ቅዱስ ነውና ይቀድሰናል ንፁህ ነውና ያነፃናል 1ጴጥ1፥15-16
ሰለዚህ እንዴት መቀደስ እንችልለን 1ዮሀ 1፥7

(9)• ከቅዱሳን ህብረት ለመደመር እንቆርባለን፦ 1ቆሮ 10፥15-17 " አንድ እንጀራ
ስለ ሆነ፥ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ
እንካፈላለንና።"
በአራቱም ማእዘን ምእመናን ተጠምቀው ልጅነት የሚያገኙበት ውሀ አንድ ማየገቦ
(በእለተ አርብ ከጎኑ የፈሰሰው ውሀ) እንደሆነ ሁሉ በአራቱም ማእዘን በቅድስት
ቤተክርስቲያ የሚሰዋው አንድ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ ይህ ማእድ ከቅዱሳን
ህብረት አንድ የሚያረገን ቅዱስ መአድ ነው።
የሚገርመው ይህ መአድ ዋጋ ያላወጣንበት (ያልከፈልንበት) ነገር ግን እጥፍ ዋጋ
የምንቀበልበት ታላቅ መአድ ነው።
እስቲ ተመልከቱ የትኛው ሆቴል ወይም ካፌ ሄዳችሁ ነው ግሩም ምግብን
ተመግባችሁ ሳትከፍሉ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብላችሁ የምትወጡ የትኛውስ
ድግስ ቤት ነው ነዳያን ከባለፀጎች በአንድ የሚመገቡ እሱ ፊት ግን ሁሉ እኩል ነው
እንዲህ ያለ የፍቅር መእድ ነው ከዚህም አልፎ ስጋውን ስለበላን ደሙንም
ስለጠጣን ዋጋ ይከፍለናል ። ት.ኢሳ 55፥1-3 እናንተ የተጠማችሁ ወደ ውሀ ኑ ያለ
ዋጋ ብሉ ጠጡ ነው የሚለው።
ይህን ሁሉ መባረክ የምናተርፍበት ከሆነ እኛ መቼ ነው መቀበል
ያለብን ? ወጣቶችም ሽማግሌዎችም ወንዶችም ሴቶችም ባለትዳሮችም
ላጤዎችም ልናስብበት ግድ ይለናል ። የመዳን ቀን ዛሬ ነው 2ቆሮ6፥2።
መቀበል የሚገባቸው እነማን ናቸው ?
በክርስቶስ የባህርይ አምላክነት ያመነ፣ ሐይማኖታዊ ምስጢር የገባው፣ ንስሃ
የገባና የተሰጠውንም ቀኖና በሚገባ የፈጸመ ክርስቲያን እድሜና ጾታ ሳይለይ
ከምስጢረ ቁርባን መካፈል ይችላል። (ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ የቅዳሴው ልዑካን
ከቤተልሔም ወደ መቅደስ ሲገቡ እንዲህ ይላሉ) "ሃሌ ሉያ እመቦ ብእሲ
እምዕመናን ዘቦአ ቤተ ክርስቲያን በጊዜ ቅዳሴ ወኢሰምዐ መጻሕፍተ ቅዱሳተ
ወኢተአገሰ እስከ ይፈፅሙ ፀሎተ ወቅዳሴ ወኢተመጠወ እምቁርባን ይሴደድ
እምቤተ ክርስቲያን .....ትርጓሜው
ሃሌ ሉያ በቅዳሴ ጊዜ ከምእመናን ወገን ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ሰው ቢኖር
ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰምቶ የቅዳሴውን ጸሎት እስኪጨርሱ ባይታገሥ፤ ከቁርባንም
ባይቀበል ከቤተ ክርስቲያን ይለይ። የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና፤ የነፍስና
የሥጋ ንጉሥ በሚሆን በሰማያዊ ንጉሥ ፊት መቆምንም አቃሏልና። ሐዋርያት
በሲኖዳሳቸው እንዲህ አስተማሩን።"
ሰለዚህ መለየት እንዳይሆንብን እራሳችንን ለካህን እያስመረመርን መቀበል
ይገባናል። በግብፅ ቤተክርስቲያን ያስቀደሰ ሁሉ ተቀድሶ (ቆርቦ) ነው የሚወጣ ።
የኛን ስንመለከት ግን ተቃራኒ ነው አንድ ወቅት በረከታቸው ይደርብንና ቅዱሱ
አባታችን አቡነ ሺኖዳ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ጊዜ እሳቸውን ለማየት ሰው መጥቶ
የቤተክርስቲያኑ ግቢ በሰው ተጨናንቋል ታዲያ እሳቸው በቅዳሴ ሳሉ ምን
አሳስቧቸው ነበር መሰላችሁ
"ይህን ሁሉ ህዝብ መቼ ነው አቁርበን የምንጨርሰው ይሉነበር" ነገር ግን ድርገት
ሲወርድ ባዩት ነገር በጣም ነው የተገረሙት የቆረቡት ሰዎች ያለውን ሩብ
አይሆኑም ነበር በጣም ነው ያዘኑት።እውነት ነው የኢትዮጵያ ህዝቦች ከግራኝ ወረራ
በፊት ያስቀደሰ ሳይቆርብ እንደማይወጣ አንዳንድ መረጃ አለ ያንንክፍተት መሰረት

አድርጎ በተናፈሰ በመንደር ተራ ወሬ ኢትዮጵያውያንና ቅዱስ ቁርባን እንደትለያዩ
እንረዳለን ነገር ግን ቅድስ ቁርባን ተቀበልንም አልተቀበልንም ሀጥያት ሞትን
እንደሚያስከትል ሮሜ 6፥23 ግልፅ ነው ሰለዚህ ህይወት እንዲበዛልን (ዮሀ
10፥10) የክርስቶስን ቅድስ ስጋና ክቡር ደሙን እንቀበል።
የቅዱስ ቁርባን ጥቅም ይህ ከሆነ በየስንት ጊዜው እንቀበል ? ከተቻለ
በየሳምንቱ እሁድና በታላላቅ በአላት ቀን ይህ ካልተቻለ በየ40 ቀኑ ይህ ካልተቻለ
በአመት ሶስቴ በልደት በትንሳኤና በጥምቀት በአላት እንዲሁም በንስሀ እራሳችንን
ለካህን ባስመረመርንበት ወቅት መቀበል ተገቢ ነው ያለ በጉ ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም መመለስ ስለሌለ። (ሉቃ15፥

☞ ከመረቁባችን በፊት ሊደረጉ የሚገባቸው ቅድመ ዝግጅቶች ☜

- ንስሐ መግባት፣ እራስን ለካህን ማሳየትሐማስመርመር፣ ቀኖና ተቀብሎ በሚገባ
መፈጸም ይገባናል። ንስሐ ሳይገባ በድፍረት መቀበል ግን እንደ በደል
ይሆንብናልና። 1ኛ ቆአፍ 11፡27
- በሚቆረብበት ቀን እንቅፋትሐመሰናክል ቢያጋጥመን ለምሳሌ. ነስር፣ እንቅፋት፣
ትውከት፣ ወደ አፍ የሚገባ ትንኝ፣ ዝንብ... ቢያጋጥመን፤ በዚያን ቀን ሊቆረብ
አይገባም፤
- ለወንዶች ዝንየትሐህልመ ለሊት ፤ ለሴቶች የወር አበባ ከታየን በዚያን ቀን ስጋ
ወደሙን መቀበል ክልክል ነው።
- ስጋዊ ንጽህና /ሰውነትን መታጠብ፣ ንጹህ ልብስእሬት መልበስ፣ ነጠላ
ማጣፋት.../
- ከመቁረባችን ከሶስት ቀን በፊት ከግብረ ስጋ ግንኙነት መታቀብሐመከልከል
አለብን
- አፋችንን እሬት እስኪለን ድረስ /ለአስራ ስምንት ሰዓታትሐመፆም የክርስቶስን
መከራ ሕማማት መስቀል አሰብን የሚያሰኘንም አንዱ ይህ ነውና

☞ከቆረብን በኋላ ማድረግ የሚገባን ጥንቃቄ✍

.

-በሚቆርቡበት ጊዜ እንደ ተራ ምድራዊ ምግብ አብዝቶ ማላመጥ (ማኘክ) አይገባም ምክንያቱም መለኮት ያልተለየው
የክርስቶስ ትኩስ አማናዊ ቅዱስ ስጋና ደም ነውና እንደተራ ምግብ ሊያላምጡት አይገባም። /ድርሳነ መድኃኒዓለምሐ

- ልክ እንደቆረቡ አፍን በነጠላሐቢ መያዝ ያስፈልጋል፤ ቀጥሎ የቅዳሴ ጸበል
መጠጣት (የቅዳሴ ጸበል አገልግሎት ስጋ ወደሙን ለተቀበሉ (ፍትሐ ነገሥት
አንቀጽ 13) እና ለድውያንሐሕሙማንሐ(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 14) ፤ ሲሆን ስጋ
ወደሙን ለተቀበሉት ሰዎች የሚሰጠው ግልጋሎት የተቀበሉት ስጋና ደም አፋቸውና
በጥርሳቸው ላይ ቀርቶ ወደ ውጪ እንዳይነጥብ ለቃልቆሐተጉጥመምጦሐ
ለማውረድ ብቻ ነው። ይህም በቅዳሴ ጸበል እንጂ በሌላ ሊፈጽሙት አይገባም
(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 13፡52)

-ልክ እንደቆረቡ አፍን በእህል ሳያድፉ ማለትም ምግብ ሳይቀምሱ ማውራት አይገባም።(ራዕየ ማርያም)

- አብዝቶ መብላት፣ መጠጣት፣ሰውነትን መብጣት፣ መነቀስ፣ ደም ቀድቶ ማውጣት ፣ጥፍር መቁረጥ፣ ጸጉር መላጨት፣ ከልብስ
መራቆት አይቻልም።

- ከቆረብን በኋላ ለሁለት ቀን ከግብረ ስጋ ግንኙነት መታቀብሐመከልከልሐመራቅ
አለብን
- ከተቆረበ በኋላ በተለይም ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ እንቅፋትሐመሰናክልሐክል
ቢያጋጥመን ለምሳሌ. ነስር፣ እንቅፋት፣ ትውከት፣ ወደ አፍ የሚገባ ትንኝ፣ ዝንብ...
ቢያጋጥመን፤ ንስሃ ልንገባና ያጋጠሙንን እክሎች በሙሉ ለካህንሐለንስሃ
አባታችንሐልንናገር ይገባል።የተሰጠንን ንስሃም ሳንፈጽም ዳግም መቁረብ
አይፈቀድምሐአይገባም።
- ሩቅ መንገድ መሔድ፣ መስገድ፣ አይገባም። ይህም ምስጢሩ፡- በስጋ ወደሙ
ድካም የለበትምና። አንድም በመንግስተ ሰማይ ከገቡ በኋላ ድካም የለምና
አንድም ድኅነት በስጋና በደሙ ሳይሆን በትሩፋት ነው እንዳያሰኝ ነው።

- ተላምጠው የሚተፉ ነገሮች እንደ ማስቲካ፣ የሽንኮራ አገዳ፣ የተለያዩ ፈራፍሬና
አትክልቶች መብላት አይገባም።

☞ቁርባን ለሚቀበሉ እንዲህ ይበሉ (ይፀልዩ) ☜

የሁሉን ልብ የምታውቅ በቅዱሳን መካከል የምትኖር ቅዱስ አምላክ ሆይ ሀጢያት የሌለብህ አንተ ብቻ ነህ ሀጢአት የምታስተሰርይ ይቅርባይም አንተ ነህ። አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ ደስ የሚያሰኝህ መስዋእት የልጅህ ስጋ እነሆ በዚህም ሀጢአቴን ሁሉ አቅልልኝ ስለ እኔ አንድ ልጅህ ሞቷልና ስለ እኔ በቀራኒዮ የፈሰሰ ንፁህ የሚሆን የመሲህም ደም እነሆ ስለ እኔ ይጮሀል ይህ የሚናገር ደም የእኔን የባርያህን ሀጢአት የሚያስተሰርይ ይሁን ስለ እነርሱም ልመናዬን ተቀበል ወዳጅህ ስለ እኔ ጦርንና ቅንዋትን ተቀብሏልና ደስ ያሰኝህም ዘንድ ታመመ ከዳንኩም በኋላ ሰይጣን ወደ ልቦናዬ ተመልሶ በፍላፃቹ ወጋኝ አቤቱ ምህረትህን ስጠኝ ፅኑ ከሳሽ ነውና ሀጢአትንም ምክንያት አድርጎ ገደለኝ እኔን ከህይወቴ ማሳትን በቃኝ ከማይል ደፋር አድነኝ አቤቱ ንጉሴና አምላኬ መድሀኒቴም የምትሆን አንተ የእኔን የባርያህን የነፍሴንና የስጋዬን ቁስል አድርቅልኝ። ጌታ ሆይ ለዚህ የተቀደሰ ምስጢር አለመግባቴን አውቃለሁ በክብርህ ፊት ልቀርብና አፌን እከፍት ዘንድ አልደፍርም ነገር ግን በይቅርታህ ብዛት ፀጋህን ሰጥተህ ለክብርህ የተገባሁ አድርገኝ መተላለፌን ሁሉ ይቅር በለኝ።
"አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ርኩስት ከሆነች ከቤቴ ጠፈር በታች ትገባ ዘንድ የሚገባኝ አይደለም።እኔ አሳዝኜሃለሁና በፊትህም ፉክ ሥራ ሠርቻለሁና በአርኣያህና በአምሳልህ የፈጠረኸዉ ሥጋዬንና ነፍሴን ትእዛዝህን በማፍረስ አሳድፌአለሁና ሥራም ምንም የለኝምና።ነገር ስለ መፍጠርህና እኔን ለማዳን ሰዉ ስለ መሆንህ ስለ ክቡር መስቀልህም ማሕየዊት ሰለ ምትሆን ስለ ሞትህ በሦስተኛው ቀን ስለ መነሣትህም ጌታዬ ሆይ ከበደልና ከመርገም ሁሉ ከኃጢአትና ከርኵሰትም ሁሉ ታነጻኝ ዘንድ እለምንሃለሁ እማልድሃለሁም። የቅድስናህንም ምስጢር በተቀበልሁትጊዜ ለወቀሳ ለመፋራረጃ አይሁንብኝ ማረኝ ይቅርም በለኝ እንጂ። የዓለም ሕይወት ሆይ በርሱ የኃጢአቴን ሥርየት የነፍሴንም ሕይወት ስጠኝ እንጂ። በሁለት ወገን ድንግል በምትሆን በወለደችህ በእመቤታችን በቅድስት ማርያም በመጥምቁ ዮሀንስም አማላጅነት በቅዱስ ሚካኤል በቅዱስ ገብርኤል ጥበቃና ተራዳኢነት ክቡራን በሚሆኑ በመላእክትም በሰማእታትም ሁሉ ፀሎት እስከ ዘለአለሙ ድረስ አሜን።"
{ ቅዳሴ ሐዋርያት}

•❖• ከቆረብን በኋላ •❖•

የከፈለልንን ውለታ ብድራቱን እያሠብን ከመዝሙረኛው ዳዊት ጋር እንዲህ እያልን ልናመሰግን ይገባል።

(መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 30)
አቤቱ፥ ተቀብለኸኛልና፥ ጠላቶቼንም ደስ አላሰኘህብኝምና ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ።
አቤቱ አምላኬ፥ ወደ አንተ ጮኽሁ ምሕረትም አደረግህልኝ።
አቤቱ፥ ነፍሴን ከሲኦል አወጣሃት፥ ወደ ጕድጓድም እንዳልወርድ አዳንኸኝ።
ቅዱሳን ሆይ፥ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፥ ለቅድስናውም መታሰቢያ አመስግኑ።
ቍጣው ለጥቂት ጊዜ ነው፥ ሞገሱ ግን ለሕይወት ዘመን፤ ልቅሶ ማታ ይመጣል፥ ጥዋት ግን ደስታ ይሆናል።
እኔም በደስታዬ። ለዘላለም አልታወክም አልሁ።
አቤቱ፥ በፈቃድህ ለሕይወቴ ኃይልን ሰጠሃት፤ ፊትህን መለስህ፥ እኔም ደነገጥሁ።
አቤቱ፥ ወደ አንተ ጠራሁ፥ ወደ አምላኬም ለመንሁ።
ወደ ጥፋት ብወርድ በደሜ ምን ጥቅም አለ? አፈር ያመሰግንሃልን? እውነትህንም ይናገራልን?
እግዚአብሔር ሰማ ማረኝም፤ እግዚአብሔር ረዳቴ ሆነኝ።

ክብሬ ትዘምርልህ ዘንድ ዝምም እንዳትል ልቅሶዬን ለደስታ ለወጥህልኝ፥ ማቄን ቀድደህ ደስታንም አስታጠቅኸኝ። አቤቱ አምላኬ፥ ለዘላለም አመሰግንሃለሁ።

ከሽማግሌዎቹም አንዱ ተመልሶ። እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው?
ከወዴትስ መጡ? አለኝ እኔም። ጌታ ሆይ፥ አንተ ታውቃለህ አልሁት። አለኝም።
እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፥ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም
አነጹ።ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፥ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ
ያመልኩታል፥ በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል። (ራ.ዮሀ
7፥13፥15) አሜን
ቅ.ዮሀንስ አፈወርቅ እንዲህ አለ "አይሁድ መፅፍትን ይፅፋሉ እኛ ግን እናነበዋለን ፤
አይሁድ መፅሀፍትን ያነባሉ እኛ ግን እንተረጉመዋለን ፤ አይሁድ መፅሀፍትን
ይተረጉማሉ እኛ ግን እንኖርበታለን" ይሄ ነውና የክርስቲያን ብልጫው ቅዱስ
ስጋውን በልተን ደሙን ጠጥተን ነጩን እንዲደርብልን መንግስቱን እንዲያወርሰን
ቅዱስ ፈቃድ ይሁን ። ክቡር ዳዊት በትንቢት “እግዚአብሔርሰ ገሃደ ይመጽእ፤ ወአምላክነሂ ኢያረምም። እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል፤ አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም።” መዝ. 49:3 እንዳለ ጌታችን በብዙ ክብርና በብዙ ኃይል ከሰማይ መላእክት ጋር ግልጥ ሆኖ ይመጣል። በዚያን ጊዜ ከመጀመሪያዉ ሰዉ ከአዳም ጀምሮ እስከ መጨረሻዉ ሰዉ ድረስ ሁላችንም በሕይወተ ሥጋ በነበርንበት ጊዜያችን የሠራነዉን ሥራ ይዘን በፊቱ እንቀርባለን (2ቆሮ. 5:10)። ጌታችንም በጎ የሠሩትን ቅዱሳን በቀኙ፤ ክፉ የሠሩትን ኃጥአንን በግራዉ ያቆማቸዉና ፍርዱን ያስተላልፋል(ማቴ. 25:31 እስከ ፍጻሜ)። በዚህ ዓለም ፈቃድ የተጓዙ ኃጥአን ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና ይጣላሉ መፅሐፍ እንዳለ "ዳሩግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም ፣የነፍሰ ገዳዮችም ፣የሴሰኞችም ፣የአስማተኞችም ፣ጣኦትንም የሚይመልኩ ፣የሐሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባህር ነው ይህም ሁለተኛው ሞት ነው" ዮሀ.ራ 21÷8። በዚህ ዓለም ክፉ ሥራ መንፈሳቸዉን እያስጨነቁ በእምነትና በቅድስና የኖሩ ጻድቃን ደግሞ በደስታ እየዘመሩ ወደማታልፈዉ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ይገባሉ።ከዚያ በኋላ ሐዘን የለም፤ ሀብታምና ድሃ የለም፤ኃይለኛና ደካማ የለም፤ በማያልቅ ደስታ ለዘላለም እንደ ቅዱሳን መላእክት ሕያው ሆኖ መኖር እንጂ።ያን ጊዜ የእኛ እጣ በየት ይሆን?በቀኙ ለመቆም እንዲያበቃን ዛሬ እንጋደል። የቅዱሳን ሐዋርያት መልእክት ፦“ወደ እግዚአብሔር መንግስት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል…” ሐዋ. 14:22 እንዲሁም፦“ጻድቅ በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመጸኛዉና ኃጢአተኛዉ ወዴት ይታይ ዘንድ አለዉ?” 1ጴጥ.4:18 ስለዚህ ትጋትን ገንዘብ አድርገን ወደ መዳን አንድንገሰግስ ቅዱስ መንፈሱ ይምራን። አሜን ወስብሐት ለእግዚአብሔር " በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም
እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን አሉ።"(ራ.ዮሀ 7:12)
የእግዚአብሔር ቸርነት የእመብርሀን ምልጃ ፀሎት የቅዱሳንና የመላእክት
ተራዳይነት አይለየን አሜን

4/13/2008ዓ.ም